# የኮሎራዶ የሕፃናት ተሳፋሪዎች ደህንነት ሕጎች

ጁን 2024 ላይ፣ በሀገረ ገዥ Jared Polis የተፈረመው ሕግ የኮሎራዶ የሕፃናት ተሳፋሪዎች ደህንነት ሕግ ማሻሻያ ሲሆን፣ ለሕፃናት የመኪና ላይ ወንበር፣ ለልጆች የወንበር ከፍ ማድረጊያ፣ እና የደህንነት ቀበቶ አጠቃቀም የቅርብ ጊዜውን በጥናት ላይ የተመሰረቱ ምክረ ሀሳቦችን የሚያንፀበርቅ ነው። ከጃንዋሪ 1፣ 2025 ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረጉት እነዚህ ማሻሻያዎች፣ በመኪና ላይ ወንበር እና ለልጆች የወንበር ከፍ ማድረጊያ አጠቃቀም ላይ እየተሻሻሉ ከመጡት ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር የኮሎራዶ ነዋሪዎች አብረው መሄዳቸውን የሚያረጋግጡ ናቸው።

**<u>የኮሎራዶ የሕፃናት ተሳፋሪዎች ደህንነት ሕጎች፣ ማሻሻያዎችን ጨምሮ በጃንዋሪ 1፣ 2025 ተግባራዊ የሚሆኑ</u>፡**

- ኮሎራዶ ውስጥ፣ አንድ አሽከርካሪ በተሽከርካሪው ውስጥ የመኪና ላይ ወንበር፣ ለልጆች የወንበር ከፍ ማድረጊያ፣ ወይም የደህንነት ቀበቶ ሳይኖረው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ልጅ በመጫኑ እንዲቆም ሊደረግ እና የቅጣት ትኬት ሊፃፍበት ይችላል።
- እያንዳንዱ የሕፃናት መገደቢያ ወይም የደህንነት ቀበቶ በአምራቹ መመሪያ መሠረት መስተካከል እና መገጠም አለበት።
- ሁሉም ልጆች ለሕፃናት መገደቢያቸው ተወስኖ የተቀመጠውን የቁመት፣ የክብደት እና የእድሜ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።
- ሁሉም የሕፃናት መገደቢያዎች የፌደራል የሞተር ተሽከርካሪ ደህንነት መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። አስመስለው የተሰሩ የመኪና ላይ ወንበሮች ይበልጥ እየተስፋፉ የመጡ ሲሆን፣ አደገኛም ናቸው። ደህንነቱ አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ በሞተር ተሽከርካሪዎች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የተሰጠው የሚል ፅሁፍ ያለበት መሆኑን ይመልከቱ።

**ወደ ኋላ የዞሩ መቀመጫዎች**

- ከ2 ዓመት እድሜ በታች፣ እና ከ40 ፓውንድ **በታች**።
- መኪናው ካለው፣ የኋለኛው ወንበር ላይ ነው መሆን ያለበት።
- ልጁ የመኪና ላይ ወንበሩን (የሚመከሩ) የቁመት እና የክብደት ገደቦችን እስኪያልፍ ድረስ፣ ከ2 ዓመት እድሜ እና ከ40 ፓውንድ በላይ ቢሆንም ወደ ኋላ ዞሮ መቀመጡን መቀጠል ይችላል።

**ወደ ፊት የዞሩ የመኪና ላይ መቀመጫዎች**

- ከ2 ዓመት እድሜ በታች፣ እና ከ40 ፓውንድ **በላይ**።
- ከ2 - 4 ዓመት እድሜ፣ **እና** ቢያንስ 20 ፓውንድ።
- መኪናው ካለው፣ የኋለኛው ወንበር ላይ ነው መሆን ያለበት።
- ልጁ የመኪና ላይ ወንበሩን (የሚመከሩ) የቁመት እና የክብደት ገደቦች እስኪያልፍ ድረስ፣ ከ4 ዓመት እድሜ እና ከ40 ፓውንድ በላይ ቢሆንም ወደ ፊት ዞሮ መቀመጡን መቀጠል ይችላል።

**ለልጆች የወንበር ከፍ ማድረጊያ**

- ከ4 - 9 ዓመት እድሜ **እና** ቢያንስ 40 ፓውንድ።
- መኪናው ካለው፣ የኋለኛው ወንበር ላይ ነው መሆን ያለበት።
- ልጁ ለልጆች የወንበር ከፍ ማድረጊያ ሳይኖር በተገቢው መንገድ የደህንነት ቀበቶውን ማድረግ እስኪችል ድረስ፣ ከ9 ዓመት እድሜ በኋላም ቢሆን ለልጆች የወንበር ከፍ ማድረጊያ መጠቀሙን መቀጠል ይችላል።

**የደህንነት ቀበቶዎች**

- ከ9 -18 ዓመት እድሜ።
- የደህንነት ቀበቶውን በተገቢው መንገድ ማድረግ መቻል አለበት።

ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎ የመኪና መቀመጫዎች ኮሎራዶ አስተባባሪዎችን በ carseatscolorado@gmail.com ያነጋግሩ።